# ደንብ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ሠነዶች፡- COA, COA-RA, COB-RA, IJA, JHE-RA

ኃላፊነት የሚመለከተው ክፍል፡- Division of School Leadership and Improvement; Division of Specialized Support Services

## የአካዳሚክ እና የባህሪ ድጋፍ ወደሚሰጥበት ማስተላለፍ/ሪፈራል

I. ዓላማ

ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የአካዳሚክ ወይም የባህሪ ሁኔታዎችን ለማሟላት የሚያስቸግሩ ባህሪያትን ሲያሳዩ መምህራን እና ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች ተማሪዎችን ድጋፍ ወደሚያገኙበት ሪሶርስ እንዲመሯቸው የአፈጻፀም ሂደቶችን ማቋቋም።

II. ትርጉም

A. ለዚህ ደንብ ዓላማ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጤና ደህንነት ባለሙያዎች ማለት በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) በአግባቡ ፈቃድና የምስክር ወረቀት ያላቸው ወይም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተገለጹትን የትምህርት እና የሙያ ት መስፈርቶችን ያጠናቀቁ እና የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያዎች/ሳይኮሎጅስቶች፣ የትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ በትምህርት ቤት የሚገኙ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ካውንስለሮች (SBECs)፣የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኞች እና በትምህርት ቤት ውስጥ ያልሆኑ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች የሕክምና ካውንስለሮች/therapeutic counselors (ETCs) ሆነው ለመሥራት ብቁ የሆኑ ሰራተኞችን ማለት ነው።የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጤና ደህንነት ባለሙያዎች ስለ ተማሪ ባህሪ/መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች እውቀት ያላቸው ሲሆኑ የተማሪ ባህሪ ፈጣን ትኩረት የሚያስፈልገው ወይም ደጋፊ ግብዓቶች ወደሚገኙበት የማስተላለፍ ጊዜና ሁኔታ ለመወሰን የሰለጠኑ ናቸው።

B. አጋር አገልግሎት ሰጪ ማለት MCPS ከጤና አጠባበቅ ባለሙያ ጋር ለመሥራት የጽሑፍ ወይም የመግባቢያ ስምምነት (MOU) ያለው የማህበረሰብ ማህበራዊ-ስሜታዊ ወይም የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪ ሲሆን፣ በልዩ የድጋፍ አገልግሎት ክፍል (DSSS) ጥያቄ መሰረት በህግ አገልግሎት ክፍል የተዘጋጀ የአጋርነት ሚና እና ኃላፊነቶችን፣ የሪፈራል

ሂደቶችን፣ የጤና ደህንነት እቅድ ማዘጋጀትን፣ የውሳኔ አሰጣጥ ደንቦችን እና ሚስጥራዊነት እንዲሁም የመረጃ ማጋራት ፕሮቶኮሎችን ከቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ እና ለጤና አጠባበቅ ባለሙያው ተገቢ በሆነው መሰረት፣ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና ለጤና መድህን ትግበራ እና የተጠያቂነት ህግ (HIPAA) ተገቢ በሆነ መልኩ ይተገበራል።

C. በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት ቡድኖች የሚከተሉትን ይመለከታል፦

1. የትምህርት አመራር ቡድን (EMT) የተማሪዎችን ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተማሪዎችን ያቀፈ ሲሆን ይሄውም ከተማሪዎች መካከል የሚጠበቅባቸውን የትምህርት ወይም የባህሪ ሁኔታ የማያሟላ/የማታሟላ ተማሪን በተመለከተ ለሚነሱ ስጋቶች መፍትሄዎችን የሚቀይስ አካል ነው።

2. የተማሪዎች ጤናና ደህንነት ቡድኖች (SWBTs) በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚገኙ ሲሆን በርካታ ተማሪዎችን ወይም የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ሊያሳትፉ የሚችሉ የትምህርት ቤት ስጋቶችን ለመወያየት እና ለሚያቀርቧቸው ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ይሠራሉ።

3. የባህሪ ስጋት ግምገማ ቡድኖች (BTATs) ተማሪዎች በራሳቸው ወይም በሌሎች ላይ የሚሰነዝሩትን ስጋቶች ለመገምገም በዲስትሪክቱ እና በትምህርት ቤቶች ተቋቁመዋል። የአባልነት እና የኃላፊነቶች ዝርዝር MCPS ደንብ COA-RA የባህሪ ስጋት ግምገማ ውስጥ ተዘርዝረዋል።

4. ለግለሰብ ሁኔታ እንዲመች የተቀረጸ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኖች እና የሰክሽን 504 ቡድኖች በፌዴራል የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA)፣ Child Find እና1973 የተሐድሶ ህግ ሰክሽን 504 (ሰክሽን 504) እና 2008የአካል ጉዳተኞች አሜሪካውያን የማሻሻያ ህግ (ADAAA) መሰረት የአካል ጉዳተኝነት እንዳለባቸው የተጠረጠሩ እና/ወይም በሰክሽን 504 መሰረት ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ወይም ማመቻቸት ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎችን በሚመለከት የተደነገጉ ሂደቶችን ይከተላሉ። IEP ቡድኖች እና የሰክሽን 504 ቡድኖች ለአካል ጉዳተኛ ልጅ IEP ወይም ሰክሽን 504 እቅድ ለማዘጋጀት፣ ለመገምገም፣ ወይም ለማሻሻል ኃላፊነት ያለባቸውን ወላጆች/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ግለሰቦችን ያቀፈ ነው።

III. ሚናዎች እና ኃላፊነቶች

A. የመምህራን እና ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሚናዎች እና ኃላፊነቶች

1. መምህራን በትምህርት ቤት ያጤኑትን ልምዶች መወያየት እና የተማሪዎችን ባህሪ ለወላጆች/አሳዳጊዎች መግለጽ ይችላሉ፣ነገር ግን ሙያዊ ጣልቃ ገብነትን የሚመለከት ምክረሃሳብ አይሰጡም።አስተማሪ ሁኔታው የአእምሮ ወይም የማህበራዊ-ስሜታዊ የጤና ሪፈራል እንደሚያስፈልግ ካመነ፣ ተማሪው(ዋ)ን ወደ አስተዳዳሪው ወይም ወደሚመለከተው ቡድን ማስተላለፍ አለበት፤ እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጤና ደህንነት ባለሙያ ማንኛውንም ውጤት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ይወያያል።

2. አንድ ተማሪ በትምህርት ወይም በባህሪ የሚጠበቅበትን ከማሟላት ጋር የሚጋጭ ባህሪ ሲያሳይ፣ መምህራን እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ስለ ተማሪው(ዋ) አሳሳቢ ጉዳዮች እና መደረግ ያለባቸውን ድጋፎች ለመገምገም ብቁ እና የሰለጠነ ባለሙያ ወደሚገኝበት ቡድን ማስተላለፍ አለባቸው።

3. ራስን የማጥፋት ምልክቶች ከተከሰቱ ወይም በራስ ወይም በሌሎች ላይ የሚሰነዘሩ ማስፈራሪያዎች ከመሳሰሉት ድንገተኛ ሁኔታዎች በስተቀር፣ መምህራን እና ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪዎችን ባህሪ በተመለከተ በመጀመሪያ EMTs ወይም SWTBs ጋር መማከር አለባቸው።

4. የአንድ ባህሪ አስጊነት እና/ወይም በድግግሞሽ መከሰት አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ የሚያፈልግ ከሆነ፣ መምህራን እና ሌሎች ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ የአስተዳዳሪውን ወይም የድንገተኛ አገልግሎቶችን ድጋፍ ከመጠየቅ ወደኋላ ማለት የለባቸውም።

    a) አንድ ተማሪ ራስን የማጥፋት ምልክቶችን ወይም ሀሳቦችን ቢያሳይ ወይም የራሱን ወይም የሌሎችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ፣ መምህሩ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ክስተቶቹን ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ እና MCPS የደህንነት ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፣ ይሄውም COA-RA ደንብ፣ ስለ አስጊ ባህሪ ገምጋሚ ቡድኖች መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን ሂደቶች ይከተላሉ።

    a) ኦክቶበር 1991 የሜሪላንድ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሁሉም የትምህርት ቤት ሰራተኞች "ልጅ ወይም ጎረምሳ/ኮረዳ ተማሪ ራስን የማጥፋት ፍላጎት እንዳለው/እንዳላት ሲታወቅ ራስን ማጥፋትን ለመከላከል ምክንያታዊ ዘዴዎችን የመጠቀም ግዴታ አለባቸው" ሲል ደንግጓል። ሰራተኞች ተማሪው(ዋ) መዛቱ(ቷ)ን ቢክድም/ብትክድም እንኳ፣ ከሌላ ሰው የደረሳቸውን የጥቆማ መረጃ ጨምሮ ስለማንኛውም የራስን ሕይወት የማጥፋት ስጋት ለተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

በእነዚህ አጋጣሚዎች፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ወዲያውኑ ከትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ፣ ከትምህርት ቤት ካውንስለር ወይም ከትምህርት ቤቱ የስነ-ልቦና ባለሙያ ጋር መነጋገር እና MCPS ቅጽ 335-54፣ ራስን የማጥፋት አደጋ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ መሙላት አለባቸው።

B. የአስተዳዳሪ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት —-

1. አንድ ተማሪ ራስን የማጥፋት ምልክቶችን ወይም ሀሳቦችን ሲያሳይ/ስታሳይ ወይም ለራሱ(ሷ) ወይም ለሌሎች ደህንነት ስጋት ሲፈጥር/ስትፈጥር አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን መወሰን፤

2. ራስን የማጥፋት አደጋ ሪፖርት ማድረጊያ ሂደቶች፣ ደንብ COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ፤ ደንብ COA-RA የባህሪ ስጋት ግምገማ፤ እና ከህግ አስከባሪዎች ጋር የመግባቢያ ማስታወሻ ሠነድ እንዲኖር ማድረግ፤

3. ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ MCPS የደህንነት አገልግሎት ሰጪዎች፣ እና ሌሎች የሚመለከታቸው ቡድኖች ጋር መማከር፤

4. IDEA እና ADAAA ላይ በተቀመጠው መሰረት የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት የፌዴራል ህግን መከተልና ማክበር፤ እና

5. ስብሰባዎች እንደ አስፈላጊነቱ ስብሰባዎች እንዲደረጉ እና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ IEP እና የሰክሽን 504 ሂደቶችን በበላይነት መከታተል።

C. EMT/SWBT/504/IEP ቡድን ሚናዎች እና ኃላፊነቶች

1. ወደ EMT/SWBT ከመተላለፉ በፊት የተማሪው(ዋ) ባህሪ የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ ውጤት እንደሆነ ከተጠረጠረ፣ IEP/Child Find ሪፈራል በአስተዳዳሪ ወይም በአስተማሪ አማካኝነት ወደ ሰክሽን 504 ቡድን ወይም ወደ IEP ቡድን መቅረብ አለበት፣ እነርሱም እንደ አስፈላጊነቱ በፌዴራል ሕግ እና MCPS ደንብ ACG-RB፣ በቅጥር፣ በአገልግሎቶች፣ በፕሮግራሞች፣ እና በእንቅስቃሴዎች ረገድ ለአካል ጉዳተኞች ምክንያታዊ ማመቻቸቶች እና ማሻሻያዎች ይከተላሉ።

   a) የተማሪው(ዋ) ባህሪ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን በእጅጉ የሚገድብ የአካል ጉዳት ሁኔታ ውጤት

እንደሆነ ከተጠረጠረ ወደ ሰክሽን 504 ቡድን ማስተላለፍ ያስፈልጋል/ሪፈራል መደረግ አለበት። ዋና ዋና የሕይወት ተግባራት ምሳሌዎች ማየት፣ መስማት፣ መብላት፣ መተኛት፣ መቆም፣ ማንሳት፣ መናገር፣ መተንፈስ፣ መማር፣ ማንበብ፣ ማሰብ፣ መግባባት እና ማተኮርን ያካትታሉ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም።

b) የተማሪው(ዋ) ባህሪ የአካል ጉዳት ውጤት እንደሆነ ከተጠረጠረ እና በተማሪው(ዋ) የትምህርት አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ካሳደረ ወደ IEP ቡድን ሪፈራል መደረግ አለበት።

2. የሚያስጠረጥር የአካል ጉዳት በማይኖርበት ጊዜ፣ EMT/SWBT ከመምህራን፣ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች እና ከሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች የሚመጡ ጥቆማዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት እና የችግር አፈታት እና የጣልቃ ገብነት እቅዶች ተገቢ መሆናቸውን መመርመር ያስፈልጋል። ይህ ሂደት የሚከተሉትን ያካትታል፦

a) ባህሪው(ዋ)ን በሚታይ እና በሚለካ ሁኔታ መግለጽ፤

b) ከባህሪው(ዋ) ጋር በቀጥታ የተያያዘ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የጣልቃ ገብነት እቅድ ማዘጋጀት እና መተግበር፤

c) የዕቅዱን ወጥነት ያለው ትግበራ መከታተል እና የጣልቃ ገብነት ውጤታማነትን መገምገም፤ እና

d) የወላጅ/የአሳዳጊ ግንኙነቶችን ለመመዝገብ እና ሪከርድ ለመያዝ የሚያስፈልጉ ሂደቶችን መከተላቸውን ማረጋገጥ።

3. እቅዱ ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ የተማሪው(ዋ) ባህሪ በአፈጻጸማቸው ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ከቀጠለ፣ የትምህርት ቤት ቡድኖች ተማሪው(ዋ) የአካል ጉዳት እንዳለበ(ባ)ት ሊጠረጥሩ እና ሰክሽን 504 ወይም IDEA/Child Find ሂደቶችን ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ።

a) ተማሪው(ዋ) ወደ IEP ለመሣተፍ ብቁ እንዳልሆነ(ች) ከተረጋገጠ፣ IEP ቡድኑ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት ቤቱ EMT/SWBT በመምራት በግል ጣልቃ ገብነት ተግባራዊ እንዲሆን እና ክትትል እንዲደረግ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። IEP ቡድን ተማሪው(ዋ) አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን በእጅጉ የሚገድብ የአካል ጉዳት ሁኔታ

እንዳለበ(ባ)ት ከተጠረጠረ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ሰክሽን 504 ቡድን ያስተላልፋል።

b) ተማሪው(ዋ) ወደ 504 እቅድ ለማስተላለፍ ብቁ እንዳልሆነ(ች) ከተረጋገጠ፣ የሰክሽን 504 ቡድን ተማሪው(ዋ)ን የግል ጣልቃገብነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እና ለመከታተል ወደ ትምህርት ቤቱ EMT/SWBT ያስተላልፋል።

4. EMT ወይም SWBT መመሪያ መሠረት፣ MCPS የጤና ባለሙያዎች ስለ ተማሪ ባህሪ ተገቢ ቴክኒኮችን በመጠቀም ተጨማሪ መረጃ ይፈልጋሉ፣ይህም የባህሪ ምልከታዎችን፣ የተማሪ ቃለመጠይቆችን ወይም ቀጥተኛ ካውንስሊንግ ሊያካትት ይችላል።

5. MCPS የጤና ባለሙያዎች እና የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የቀውስ ማዕከል እና/ወይም በሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ፕሮግራሞች በኩል ለቤተሰቡ ያሉትን የማህበረሰብ አገልግሎቶች ማሳወቅ፣ ለወላጆች የተወሰኑ አገልግሎት አቅራቢዎችን የማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ሪፈራል ምንጮችን ዝርዝር መስጠት፣ እና ቤተሰቡ የሚታመንበት የህክምና ባለሙያ ካለው መጠየቅ እና ከዚያ ባለሙያ ጋር መማከር እንዳለባቸው ምክረሃሳብ መስጠት ይችላሉ።

D. የግል አገልግሎት አቅራቢዎች በወላጅ/በአሳዳጊ ጥያቄ ወደ ስብሰባዎች ይጋበዛሉ

1. ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ MCPS ውጭ ለተማሪ አገልግሎት የሚሰጠውን ባለሙያ ተማሪን ስለመደገፍ በሚደረግ ስብሰባ ላይ እንዲሳተፍ ሊጋብዝ ይችላል።

2. ወላጅ/አሳዳጊ ትምህርት ቤቱ ከ MCPS ውጭ የሆነ(ች) ባለሙያ ጋር ግንኙነት እንዲቀጥል ከጠየቁ፣ ቅጽ 336-32፣ ሚስጥራዊ መረጃ ለማጋራት የሚሰጥ ፈቃድ፣ በወላጅ/በአሳዳጊ ተፈርሞ ለትምህርት ቤቱ እና ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጭ ለሆነ ባለሙያ መሰጠት አለበት።

E. የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጤና ባለሙያዎች የካውንስሊንግ አገልግሎት ስምምነት

1. MCPS የጤና ባለሙያዎች ካውንስሊንግ እንዲሰጡ የወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ MCPS ቅጽ 339-1፣የግለሰብ ካውንስሊንግ ፈቃድ/ስምምነት፣ እና/ወይም MCPS ቅጽ 339-2፣ለቡድን የካውንስሊንግ ፍቃድ/ስምምነት በመጠቀም ማግኘት ይቻላል።

2. አንድ ተማሪ ከዚህ በታች እንደተገለጸው ለካውንስሊንግ አገልግሎት ፈቃድ መስጠት ይችላል/ትችላለች፦

   a) በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣ ዕድሜው 12 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሰ(ች) ልጅ፣ በጤና አጠባበቅ ባለሙያ ፈቃድ የመስጠት በቂ ችሎታ እንዳለው/እንዳላት የሚወስነው፣ ልክ እንደ አዋቂ ሰው፣ በጤና አጠባበቅ ባለሙያ ወይም ክሊኒክ አማካኝነት የአእምሮ ወይም የስሜት መቃወስ ችግር ካውንስሊንግ ማድረግ፣ ምርመራ፣ እና ሕክምና ለመስጠት ፈቃደኛ የመሆን ብቃት አለው።

   b) በሜሪላንድ ሕግ መሠረት የአእምሮ እና የስሜት መቃወስ ችግሮችን ለመመርመር እና ለማከም ባለው ፈቃድ መሠረት የሚሠራ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጤና ባለሙያ ተማሪው(ዋ) የካውንስሊንግ ፈቃድ የመፈረም ብቃት እንዳለው/እንዳላት ሊወስን ይችላል።

3. በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣IEP ጋር እንደ ተዛማጅ አገልግሎት የካውንስሊንግ አገልግሎት የሚቀበል/የምትቀበል ተማሪ ፈቃድ የመፈረም ስልጣን እንደሌለው/እንደሌላት ልብ ይበሉ። የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ተማሪው እስኪመረቅ/እስክትመረቅ፣ 21 ዓመት እስኪሞላው/እስኪሞላት ድረስ ከልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እስኪወጣ/እስክትወጣ፣ በራሱ(ሷ) ነፃ እስኪወጣ/እስክትወጣ ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች ሊገኙ እስኪችሉ እና የተተኪ ወላጅ ሂደቱ እስኪተገበር ድረስ የወላጅነት መብታቸው ይጠበቃል።

4. ከአጋር አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጤና ባለሙያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃድ ያገኛሉ።

**ተዛማጅ ምንጮች:** Annotated Code of Maryland, Health-General Article, §20-102 and §20-104.

**የደንቡ ታሪክ:** አዲስ ደንብ፣ ኦክቶበር 1982፣ ጁላይ 21, 1987 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 25, 2007 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 13, 2009 ተሻሽሏል፤ ኖቬምበር 24, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንውስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተሣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይሣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025